በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
Ethiopian Revenues and Customs Authority
የአ.አ. ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት
A.A. Comercial Goods Facilitation Branch Office

# የ ው ስ ጥ  መ ፃ ፃ ፊ ያ
INTER OFFICE MEMORANDUM

ቁጥር :- ሥ/አ/ጽ/ቤት 064/04

ቀን :- 05/04/2004

ለስራ ሂደቶች

አ.አ. ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት

ከዋናው መ/ቤት የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተርየዋጋና ታሪፍ ምደባ አሠራርና ኘሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በደብዳቤ ቁጥር 6.1.0/500/17 በ28/03/04 በተፃፈ ደብዳቤ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ ታክስ ለማስከፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር 567/2000 አንቀጽ 7 መሠረት ያወጣውን መመሪያ ቁጥር 30/2004 የገለፀበትን 13 ገጽ አባሪ አድርገን የተላከ መሆኑን እየገለፅን በስራችሁ ለሚገኙ ቡድኖችና ሰራተኞች እንዲያውቁት እና በዚሁ መሠረት እንዲፈፀም አሳስባለሁ::

ከሠላምታ ጋር

ፋሲል ታደሰ
ሥራ አስኪያጅ

ግልባጭ፣

- ለሥነ ምግባር መከታተያ ቡድን
  አ/አ/ን/ዕ/ማ/ቅ/ጽ/ቤት

ሚ.ለ/

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 6/10/500/17
Ref. No.
ቀን 28 ህዳር 2004
Date

ለመረጃ ቴክኖሎጂ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት

ለሁሉም የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤት

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ ታክስ ለማስከፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር 567/2000 አንቀጽ 7 መሠረት ያወጣው መመሪያ ቁጥር 30/2004 ከታህሳስ 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል በቁጥር ታ/ከ/ቀ/5/577 በ22/03/04 ዓ.ም በተፃፈ ሸኝነት ደብዳቤ ልኳል፡፡

የተጠቀሰውን መመሪያ 3 ገጽ ፎቶ ኮፒ ከዚህ ጋር በማያያዝ ከላይ ከተገለፀው ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ እንዲደረግ የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ታደለ ዝማርያም
ዳይሬክተር
(ቅ/ጽ/ቤቶች ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት)

ግልባጭ፡-

- ለዋና ዳይሬክቶሬት ጽ/ቤት
- ለህግ ማስከበር ስራዎች ዘርፍ
- ለኦፐሬሽን ዲዛይንና ፕሮግራም ልማት ስራዎች ዘርፍ
- ለቅ/ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለትምህርትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለዋጋ ትመናና ታሪፍ ዳይሬክቶሬት
- ለዐቃቤ ህግ ዳይሬክቶሬት

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

1494
25.3.04

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Development

ቁጥር ሃ/ካ/ቀ/5/572
Ref.No

ቀን 22/03/2004
Date

ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
<u>አዲስ አበባ</u>

ለውጭ ገቢያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ ታክስ ለማስከፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር 567/2000 አንቀጽ 7 የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በአዋጁ የተመለከተውን የማስከፈያ ልክ ለማሻሻል እንደሚችል ይደነግጋል::

በዚህም መሠረት ለውጭ ገቢያ በሚቀርብ በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ የተጣለውን ታክስ ለማሻሻል የሚያስችል መመሪያ ቁጥር 30/2000 ወጥቷል::

ስለዚህ መመሪያውን 5 ገጽ ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ ከታህሣሥ 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሳስባለን::

ከሠላምታ ጋር

ሶፍያን አህመድ
ሚኒስትር

ግልባጭ፣
ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>

Ethiopian Revenues & Customs Authority
Records & Documentation No. 2

Lett.W/G/T

13

3.8 «አዋጅ» ማለት ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ ታክስ ለማስከፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር 567/2000 ነው።

3.9 በዚህ መመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ቃላትና ሐረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

## 4. ማሻሻያ

ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ የሚከፈለው ታክስ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

ሀ) ጥሬ ቆዳና ሌጦ ከዋጋው 150%
ለ) ዌትብሉ የበሬ ቆዳ ከዋጋው 150%
ሐ) ፒክልድ የበግ ሌጦ ከዋጋው 150%
መ) ዌትብሉ የፍየል ሌጦ ከዋጋው 150%
ሠ) ክረስት የበሬ ቆዳ ከዋጋው 150%
ረ) ክረስት የበግ ሌጦ ከዋጋው 150%
ሰ) ክረስት የፍየል ሌጦ ከዋጋው 150%

## 5. ያለቀለት ቆዳ ኖርም

ማንኛውም የቆዳ አምራች ለውጭ ገበያ የሚያቀርባቸው ባለቀለት ደረጃ የተዘጋጁ ቆዳና ሌጦዎች ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን ያለቀለት ቆዳ ኖርም ያሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል።

## 6. ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ቆዳ ወይም ሌጦን በተመለከተ የሚፈለጉ መረጃዎች

ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ቆዳና ሌጦን ወደውጭ አገር ሲልክ የሚከተሉትን መረጃዎች አሟልቶ ማቅረብ አለበት።

ሀ) የቆዳ ወይም የሌጦ ምድብ የበሬ ወይም የበግ ወይም የፍየል መሆኑን፣

ለ) ቆዳው ወይም ሌጦው የተመረተበት ዓላማ ለጫማ ሽፋን፣ ለአልባሳት፣ ለጓንት፣ ለገበር ወይም ለሌላ መሆኑን፣

ሐ) የቆዳው ወይም የሌጦው የውፍረት መጠን በሚሊ. ሜትር፣

መ) የቆዳው ጥራት ደረጃ በምርጫ ውጤቱ መሠረት ከ1ኛ - 3ኛ፣ 4ኛ፣ 5ኛ፣ 6ኛ ወይም ውዳቂ ወይም A, B, C, D, E መሆኑን፣

ሠ) የቆዳው ወይም ሌጦው የቀለም ዓይነት ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ጥቁር፣ ቡናማ፣ ግራጫ፣ ወዘተ መሆኑን፣

ረ) የቆዳው የሌጦው ብዛት በቁጥር ወይም በስፋት መጠኑን በካሬ ጫማ ወይም በካሬ ሜትር የሚያሳይ ሰነድ፣

ሰ) የቆዳው ወይም የሌጦው ነጠላ ዋጋ ወይም አጠቃላይ ዋጋ በውጭ ምንዛሪ እና በብር መሆኑን የሚገልፅ መረጃ፣

## 7. <u>አዋጁንና መመሪያውን የማስፈፀም ኃላፊነት</u>

1. የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ሀ) ከአገር የሚወጡ ዕቃዎችን ለመፈተሽ፣ ለመመዝገብ፣ ለመቆጣጠር እና ታክስ ለማስከፈል በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ወደውጭ አገር የሚላኩ የቆዳና ሌጦ ምርቶችን የመፈተሽ፣ የመመዝገብ የመቆጣጠርና ታክስ የማስከፈል ተግባራትን ያከናውናል።

ለ) ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት በአዋጁና በዚሁ መመሪያ መሠረት ቀረጥ ተከፍሎበት ወደውጭ አገር እንዲላክ የተወሰነን ምርት ቀረጥ ሳይከፍል ለመላክ ቢሞክር ወይም ቢልክ በጉምሩክ አዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ጉዳዩን የመመርመር፣ የመክሰስ፣ የማስቀጣት እንዲሁም ክስ የማንሳት ተግባራትን ይፈፅማል።

2. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንደአስፈላጊነቱ ያለቀለት ቆዳ ኖርምን እየከለሰ እንዲፀድቅ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያቀርባል።

3. የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ሀ) ከተቋቋመበት ዓላማ አኳያ ይህንን መመሪያ ለማስፈፀም የሚረዱ ማናቸውም ሙያዊና ቴክኒካዊ እገዛዎችን ያደርጋል፣

ለ) ኢንስቲትዩት ከማናቸውም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ጥያቄ ሲቀርብለት ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ ከቀረበው ያለቀለት ቆዳ መስፈርት አንፃር ሲታዩ አጠራጣሪ ሆነው የተገኙ የቆዳና ሌጦ ምርቶችን መርምሮ የውሣኔ ሀሳብ ያቀርባል።

8. <u>ስለመሻር</u>

ለውጭ ገበያ በሚቀርብ የተዘጋጀ ቆዳ ላይ የተጣለውን ታክስ ለማሻሻል የወጣው መመሪያ ቁጥር 25/2001 ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል።

9. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከታህሣሥ 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ኅዳር 22 ቀን 2004 ዓ.ም

ሱፍያን አህመድ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት
ሚኒስትር

ሱፍያን አህመድ
ሚኒስትር

Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2



18

Application of foil/film — Acrylic/ PVC/PU foil or film

Rolling — The operation of rolling the heavy leathers like sole leather using a heavy roller with rolling machine.

Ministry of Finance and Economic Development
Record & Archive
Ministry of Industry
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2